ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት አስተዳደር መመሪያ

# ቁጥር -------

ነሐሴ 2015
አዲስ አበባ

የግብርና ሚኒስቴር የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት አስተዳደር መመሪያ" ቁጥር ---------ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "አዋጅ"፡ ማለት "የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1289/2015" ነው፤
2) "የመልካም ግብርና አሰራር" ማለት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና የግብርና አሰራሮችን የአፈርን ለምነትን በማይጎዱ፣ አከባቢን በማይበክሉ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ጫና በማይስከትሉበት ሁኔታ መጠቀም ነው፤
3) "የግብርና ቴክኖሎጂ" ማለት በምርምር የተገኘ በእንስሳት፣ በዕጽዋት እና በግብርና ተፈጥሮ ሃብት መስክ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም ጥራትን እና ጤንነትን ለማሻሻል የሚውል ሆኖ በባለስልጣኑ ብቁነቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ወይም በሌላ አገር ተመዝግቦ በግብርና ውሳኔ ቀጥታ የቴክኖሎጂ ስም ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የባህላዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር ግኝት ነው፤
4) "በሙከራ ደረጃ" ማለት አንድ የተሻሻለ አሰራር ወይም የግብርና ቴክኖሎጂ በሰርቶ ማሳያ ደረጃ ውጤታማነቱ እስኪረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፤
5) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ወይም በክልል የግብርና ግብዓትና ምርትን ጥራት የሚቆጣጠር ባለሰልጣን ወይም የመካኒካል ቴክኖሎጂ ወይም ደቂቀ ዘአካላት እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎችን የሚመዘግብ የፌደራል አግባብ ያለው ባለስልጣን ነው፤
6) "ቴክኒክ ግብረ ኃይል"፡ ማለት አግባብ ባለወ አካል የምርት መጠን ወይም ጥራት መቀነስ ወይም ሙሉ በሙሉ መጥፋት ወይም መጨመር መንስኤዎችን ለማጥናት ከራሱና ከሶስተኛ ወገን የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የሚደራጅ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ድጋፍ አሰጣጥ

**3. አስመራች ለአምራች ስለሚሰጠው ድጋፍ አፈጻጸም**

የግብርና ምርት ውል ዓይነቶችን መሰረት ተደርጎ የሚሰጥ ድጋፍ የሚከተሉትን ያካተተ ሊሆን ይችላል፤

1) ስለ ተቀናጅ ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ/ አስመራቹ ይዞት ከሚመጣ የግብርና ቴክኖሎጂ እና በራሱ ማሳ ከሚያሳየው የመልካም ግብርና አሰራር የተነሳ በአካባቢው እና በዙሪያው ውል ለተዋዋሉ አምራቾች የኤክስቴሽን አገልግሎት መስጠት፤

ለ/ ከሰጠው የኤክስቴሽን አገልግሎት የተነሳ ተቀባይነት ያገኙ አሰራሮችንና የግሉ የሆነ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በሙከራ ደረጃ በተመረጡ እና ማዕከላዊ ቦታዎች በሚገኙ ሞዴል አምራቾች በስፋት ማስተዋወቅ፤

ሐ/ በስፋት ለተዋወቀው የአስመራቹ የግብርና ቴክኖሎጂ እና የመልካም ግብርና አሰራር በአስመራቹ እና በአምራቹ መካከል በሚደረገው ውል መሰረት ግብዓቶች እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

2) ስለ ተማከለ ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ/ አሰምራቹ ከአምራቹ የግብርና ምርቱን የራሱን ባለሙያዎች በመቅጠር ወይም የሶስተኛ ወገን በመወከል ቀጥታ ከአምራቾች መሰብሰብ ይችላል፤

ለ/ አስመራቹ በሚመድባቸው የራሱ ቅጥር ባለሙያዎች ውል ለገባው አምራች በአመራረት እና በግብይት ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ የምርት ጥራት ቁጥጥር ሥራዎችን ይሰራል፤

ሐ/ አስመራቹ በአምራቾች አጠገብ የምርት ማዘጋጃ እና ማከማቻዎችን ሊገነባ ይችላል፤ ወይም በኪራይ ሊያመቻች ይቸላል፤

መ/ የአካባቢው አግባብ ያለው አካል አስመራቹ ለሚገነባው የማዘጋጃ እና የማካማቻ መሰረተ ልማቶች የሚሆን መሬት፣ የጸጥታ ዋስትና፣ የኃይልና የውኃ አቅርቦት ትብብር እንዲደረግ ያመቻቻል፤

ሠ/ አስመራቹ ከአምራቹ ጋር በሚገባው ውል መሰረት ግብዓቶችንና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡

3) ስለ ባለብዙ ተዋንያን ውል የድጋፍ አሰጣጥ

ሀ/ ባለብዙ ተዋንያን ውል ዓይነት የግብርና ምርት ውልን የሚደግፉ የሶስተኛ ወገንና አግባብ ያለው አካልን ያካትታል፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ሀ” የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሶሰተኛ ወገን የመንግስትና የግል የግብርና ምርምር ተቋማትን፣ ዩኒቨርስቲዎችን፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎችን፣ የፋይናንስ ተቋማትን፣ አማካሪዎችን፣ የሲቪክ ማህበራትና ድርጅቶች፤ የዘርፍና የሙያ ማህበራት፣ ሕብረት ሥራ ማህበራትን ወይም ሌሎች ድጋፍ ሰጪዎችን ሊያካትት ይችላል፤

ሐ/ ለተዋዋዮች ድጋፍ የሚሰጡ የሶስተኛ ወገን ተዋንያን የድጋፍ አሰጣጥ ሂደቱን ውጤታማ የሚያደርግ የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማሉ፤

መ/በመግባቢያ ሰነዱ የሚሳተፍ ማንኛውም ሶስተኛ ወገን በመግባቢያ ሰነዱ ለተዋዋዮች ስለሚያደርገው የድጋፍ ዓይነት በግልጽ ማስቀመጥ አለበት፤

ሠ/ በድጋፍ አሰጣጡ ሂደት አግባብ ያለው አካል ሊኖረው ስለሚገባ ድርሻ በመግባቢያ ሰነዱ በግልጽ መቀመጥ አለበት፤

ረ/ የመግባቢያ ሰነዱን አግባብ ያለው አካል ከተዋዋይ እና ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፡፡

ሰ/ የሶስተኛ ወገን ሚና የተዋዋዮችን ውል በሚጣረስ መንገድ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ያለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፤

4) ስለ አገናኝ ውል የድጋፍ አሰጣጥ፤

አገናኝ አምራቹን ሙሉ በሙሉ ወክሎ

ሀ/ ህጋዊ የግል ወኪል፤የህብረት ሥራ ማህበር፣ የዘርፍና የሙያ ማህበራት፣ የግል እና የመንግስት የትምህርት ተቋማት፣ የመንግስትና የግል የምርምር ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራትና ድርጅቶች ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን አገኛኝ ሊሆን ይችላል፤

ለ/ አምራቹ እንዲወከለው የወሰነውን አገናኝ ህጋዊነት አስመልክቶ ለአስመራቹ በቂ ማስረጃ ወይም መረጃ መስጠት አለበት፤

ሐ/ አምራቹን የሚወክለው አገናኝን ሚና ወሰን በተመለከተ ተዋዋዮቹ በውላቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

መ/ አገኛኝ ስለሚኖረው ሚና መወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ አምራች ከአስመራቹ ማግኘት በሚገባው ግብዓትና የቴክኒክ ድጋፍ ላይ አሉታዊ ሚና መጫወት የለበትም፤

4. **በሶስተኛ ወገን ስለሚሰጥ የድጋፍ ዓይነትና የአፈጻጸም መስፈርት፡**

በአዋጁ አንቀጽ 16 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአምራቹ የሚሰጡ ማበረታቻዎች የግብርና ምርታማነትና ጥራት የሚያሳድጉ ግብዓቶችን ነው፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ውልን ስለሚለውጡ ሁኔታዎች</u>

5. **ዋጋ ሲጨምርና ሲቀንስ የማሻሻያ ሁኔታዎች፡**

በምርት ርክክብ ጊዜ ከውሉ ከተገለጸው በላይ ዋጋ ሲጨምርና ሲቀንስ የማሻሻያ ሁኔታዎች፡

1) የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሁኔታ በውሉ ላይ በግልጽ አስቀምጠው ከሆነ በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤
2) የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ዝርዝር ሁኔታ በውላቸው ላይ ካላስቀመጡ ግን በሚከተሉት ሂደቶች መሰረት የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፤

ሀ/ በወቅታዊ ዋጋ ላይ ልዩነት ሲኖር ሁለቱ ወገኖች በጋራ በመነጋገር በስምምነት መፍታት ይችላሉ፤

ለ/ ከላይ በተራ ፊደል “ሀ” የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጡት አንድ የጋራ አደራዳሪ አማካኝነት ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፤

ሐ/ ከላይ በተራ ፊደል “ለ” በተገለጸው መሰረት በአደራዳሪው አማካይት መግባባት ላይ ካልደረሱ ተደራዳሪዎቹ የየራሳቸውን አንድ አንድ ሰው መርጠው የሚመለከተው አግባብ ያለው አካል ሊያደራድራቸው ይችላል፤

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ “ሀ እስከ ሐ” በተደነገገው ሰምምነት ላይ ካልደረሱ በአዋጁ መሰረት በፍርድ ቤት ይዳኛሉ፡፡

6. **ምርት መጠን ሲቀንስ ወይም ሲጨመር የውል አፈጻጸም ሁኔታዎች፤**

አምራቹ እና አስመራቹ በውል ስምምነታቸው መሰረት የምርት ግምት ተካሂዶ፡

1) በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ በውሉ የተጠቀሰው ምርት መጠን ቢቀንስ አምራቹ ውል እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ/ በአስመራቹ የተሰጠውን የግብርና ቴክኖሎጂ መጠቀም ትቶ ከውሉ ውጭ ሌላ የተጠቀመ እንደሆነ፤

ለ/ በአስመራቹ በተሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ መሰረት ሳይጠቀም ሲቀር፤

ሐ/ ምርቱን ከሰበሰበ በኂላ ሆን ብሎ ለራሱ ሲያስቀር ወይም ለሌላ ወገን ሲሸጥ፤

መ/ በአስመራችና አምራች ውል የተጠቀሱና በአምራቹ ሊተገበሩ የሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮች ሳይተገበሩ ሲቀሩ፤

ሠ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል “ሀ” እስከ “መ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

2) በሚከተሉት ምክንያቶች በውሉ ከተጠቀሰው በታች ምርት ቢቀንስ አስመራቹ ውል አንደተጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ/ ለአምራቹ የሰጠው የግብርና ቴክኖሎጂ በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ያልተመዘገበ ወይም ውጭ ሃገር ተመዝግቦ በሃገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፤

ለ/ ለአምራቹ የሰጠው የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ተባይ ወይም በሽታ መከላከያ መድሃኒት በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ወይም ውጭ ሃገር ተመዝግቦ በሃገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ ያልተመዘገበ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፤

ሐ/ ለአምራቹ ሊሰጠው የሚገባ የግብዓት ወይም የቴክኒክ ድጋፍ በግብርና ምርት ውሉ በተቀመጠው ጊዜ፣ ጥራት እና በሚፈለገው መጠን ልክ ሳይሰጥ ሲቀር፤

መ/ በተዋዋዮች የግብርና ምርት ውል ላይ የተጠቀሱ እና ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ እና ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ሌሎች ግብዓቶች እና አሰራር በአስመራቹ ለአምራቹ ሳይሟሉ ሲቀሩ፤

ሠ/ አስመራቹ በስነልክ ኢንስቲቱት አግባብነታቸው ያልተረጋገጠ ሚዛን ወይም ሌላ መለኪያ በመጠቀሙ፤

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል “ሀ” እስከ “ሠ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ኃይል የተነሳ ምርትና ምርታማነት ቢቀንስ በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

4) የምርት መጠን በሚከተሉት ምክንያቶቸ አምራቹ ጨምሮ ሲገኝ ውል እንደተጣሰ ይቆጠራል፡

ሀ/ በውል ከተያዘው ማሳ ውጭ የተሰበሰበ ምርት ከተጨመረ፤

ለ/ የግብርና ምርት ማምረት ውልን ዓላማን በሚጻረር መልኩ ምርታማነት እንዲጨምር ከተደረገ፤

5) አምራች አሰመራች ባልገመተው ሁኔታ ሙሉ የአመራረት ምክረ ሃሳብ ጥንክርና አሰራር ተጠቅሞ ውል ከተገባው ምርትና ምርታማት ጨምሮ ቢገኝ አስመራች ስለሚገዛበት ሁኔታ በውሉ መካተት አለበት፡፡

## 7. የምርት ጥራት ሲጓደል የአፈጻጸም ሁኔታዎቸ፡-

ለምርት ጥራት መጓደል መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ በግብርና ምርት ውል ውስጥ ማካተቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) በሚከተሉት ምክንያቶች የምርት ጥራት መጓደል ቢከሰት አምራቹ ግብርና ምርት ውሉን እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤ ፤

ሀ/ ሆን ብሎ ባዕድ ነገሮችን በግብርና ምርቱ ውስጥ ከጨመረ፤

ለ/ ሆን ብሎ ውሃ በመጨመር የተፈቀደው የተፈጥሮ የእርጥበት መጠን ወይም ይዘት ካዛባ፤

ሐ/ ከተፈቀደው የግብርና ምርት መያዣ ወይም መሰብሰቢያ ወይም ማከማቻ ወይም ማጓጓዣ ወይም ማቀዝቀዣ ውጭ ወይም ምርቱን በማስቀመጡ ወይም በማጓጓዙ ጥራት ሲያጓድል፤

መ/ ተገቢውን የጸረ ተባይ ወይም የበሽታ መከላከያ መድሃኒት ባለመጠቀሙ የምርቱ ጥራት ቢጓደል፤

ሠ/ ያልተፈቀደ ወይም በተዋዋይ ወገኖች ውል በግብርና ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ይዘት እና ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል ከተጠቀመ፤

ረ/ ሌሎች በግብርና ምርት ውሉ የተጠቀሱ ወይም በተክኒክ ድጋፍ ወቅት በጽሁፍ የተገለጹ ጥራትን ሊጠብቁ የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦች በአምራቹ በኩል ተግባራዊ ሳይሆኑ ሲቀሩ፤

ሰ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል "ሀ" እስከ "ረ" የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

2) በሚከተሉት ምክንያቶች የምርት ጥራት መጓደል ቢከሰት አስመራቹ የግብርና ምርት ውሉን አንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት ይወስዳል፤

ሀ/ በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችሉ ግብዓቶች ለአምራቹ ሳያቀርብ በመቅረቱ፤

ለ/ በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ ለአምራቹ ሳይሰጥ ቢቀር፤

ሐ/ ያልተፈቀደ ወይም ግዜ ያለፈበት ወይም በግብርና ምርት ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል አምራቹ አንዲጠቀም ካደረገ፤

መ/ በውሉ በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ተገኝቶ ምርቱን ከአምራቹ ባለመረከቡ በሚደርስ የምርት ጥራት መጓደል፤

ሠ/ ሌሎች ጥራትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እና በግብርና ምርት ውሉ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈጽም ቢቀር፤ እና

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል "ሀ" እስከ "ሠ" የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋር የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

3) "ባዕድ ነገር" ማለት በሃገሪቱ የግብዓትና ምርት ጥራት ደረጃዎች መሰረት ጥራት የሚያጓድሉ ተበለው ከተፈላጊወ ቁስ የተለዩትን ሁሉ ያከትታል፡፡

## 8. ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሲፈጠር የማሳወቂያ ሂደት አፈጻጸም እና የግዜ ገደብ

ከግብርና ምርት ተዋዋይ ወገኖች በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በተፈጠረ ጊዜ፡

1) ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በ 48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

2) የተከሰተውን ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በስልክ፣ በኢመይል፣ በጽሁፍ መልዕክት ወይም በአካል ማሳወቅ አለበት፤

3) የተከሰተውን የጉዳት መጠን ለመወሰን ሁለቱ ወገኖች በጋራ በመነጋገር በስምምነት መፍታት ይችላሉ፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ "3" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጡት አንድ የጋራ አደራዳሪ አማካኝነት ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፣

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "4" በተገለጸው መሰረት መግባባት ላይ ካልደረሱ ተዋዋዮች የየራሳቸውን አንድ ሰው መርጠው ሦስተኛ ወገን በተገኘበት አግባብ ያለው አካል ሊያደራድራቸው ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

### 9. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

አንድ ሰው በግብርና ውል ተመስርቶ የግብርና ምርትን ለማምረት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች እንዲሰማራ ሲጠይቅ የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያረጋግጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

1) በግብርና ምርት ውል ለመሳተፍ በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣
2) የታደሰ የኢንቨስትመንት ፍቃድ፤
3) የታደሰ ንግድ ስራ ፍቃድ፣
4) ለህበረት ሥራ ማህበራት ሲሆን የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
5) በሚሰማራበት ወረዳ አግባብ ባለው አካል የተፈረመና ማህተም ያረፈበት የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ ማቅረብ የሚችል፤
6) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረት እና ለመግዛት ከሚገባው ምርት ጠቅላላ የመግዣ ዋጋ አስር በመቶ በዝግ አካውንት ሰለማስያዙ፤
7) አስመራች፡
   ሀ/ ያስመረተውን ምርት  ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት በገባው ውል መሰረት ከአምራቹ በግዢ መረከብ እንደሚችል የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ ላይ በግልጽ የሰፈረ መሆኑ ሲረጋገጥና
   ለ/ ቅጹ በወረዳ አግባብ ያለው አካል የተፈረመበትና ማህተም ያረፈበት ሲሆን፣
   ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ “ለ” ስር የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል የማጠቃለያ ቅጽ በክልል አግባብ ባለው አካል አባሪ ደብዳቤ ለሚኒስቴሩ የተላከ መሆኑን ሲረጋገጥ፤
8) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-7 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አነስተኛ ይዞታ ካላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ለማምረት የሚሰማራ ከሆነ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤
   ሀ/ ለአርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሰጠውን የግብዓትና የቴክኒክ ድጋፍ በሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል ቅጽ ላይ በቀረበው የግብዓትና የቴክኒክ ድጋፍ ማጠቃላይ ክፍል ላይ በግልጽ መስፈሩ ሲረጋገጥ፣
   ለ/ አስመራች የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርት መሰብሰብ የሚያስችለው ተሽከርካሪ፣ የኢትዮጵያን ደረጃ ያሟላ መጋዝን እና በግብርና ነክ ሳይንስ ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የሰለጠነ ባለሙያ ያለው መሆኑን፤ወይም
   ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደለ ተራ “ለ” ስር የተገለጸውን አገልግሎት አስመራቹ በሶስተኛ ወገን በኩል ለማከናወን የሚያስችል ውል መግባቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከሚመለከተው ባለስልጣን ማቅረብ የሚችል፤

### 10. በክልል ደረጃ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

ማንኛውም ሰው በአንድ ክልል ብቻ በግብርና ምርት ውል መሰረት ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲፈልግ ከክልሉ አግባብ ያለው አካል የሚያገኝ ሆኖ፤

1) በክልሉ አግባብ ያለው አካል የአምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን ያወጣውን መመሪያ መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል፤

2) የክልሉ አግባብ ያለው አካል የሚያወጣቸው መስፈርቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 ከተገለጹት መስፈርቶች ጋር እንዲስማሙ ማድርግ ይችላል፤

**11. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሰው መብት**

በግብርና ምርት ውል መሰረት ለማምረት የግብርና ሚኒስቴርን ወይም የክልል አግባብ ያለውን አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው አስመራች፡

1) ውል ከገባላቸው አምራቾች ጋር በቀጥታ የመገናኘት፣ ሰብስቦ የመወያየት፣ ስልጠና የመስጠት፣ የመከተታልና ድጋፍ የመስጠት መብት ይኖረዋል፤
2) ስራውን የሚያከናውንበትና ከአምራቾች ምርት ለመሰብሰብ የሚያስችለውን መጋዝንና ጽ/ቤት ለመገንባት የሚሆን የመሬት ይዞታ ከአካባቢው የመንግስት አስተዳደር የማግኘት መብት ይኖረዋል፤
3) ስራውን በሚያከናውንበት የሥራ አካባቢ ከአካባቢው አስተዳደር የደህንነትና የጥበቃ ዋስትና የማግኘት መብት ይኖረዋል፤
4) ውል ከገቡለት አምራቾች ምርቱን እንዳይሰበስብ እንቅፋት ከሚሆንበት ወይም ምርቱን ከሚሻማው ማንኛውም ሰው በአካባቢው የአስተዳደርና የጸጥታ ኃይል ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፤

**12.የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል የአምራች ማጠቃለያ ቅጽ ይዘት**

ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች በግብርና ምርት ውል ተመስርቶ ለማስመረት ለሚሰማራ ሰው የሚዘጋጀው የሚኒስቴሩ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ ቢያንስ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፤

1) የአስመራች ሰም እና አድራሻ
2) የተመዘገበበት የንግድ ፈቃድ ቁጥር የሀብረት
3) ለአርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሰጠው የድጋፍ ዓይነት የሚያሳይ መረጃ፤
4) የሀብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የተመዘገገበበት የምስክር ወረቀት፤
5) አስመራች የግብርና ምርት ውል የገባባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች ዝርዝር ለወረዳ አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤
6) የግብርና ማምረት ተግባሩ የሚከናወንበት ቦታ አድራሻ የሚያሳይና በጂፒኤስ የተደገፈ ካርታ ለወረዳ አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤
7) በውሉ የተካተቱ አምራቾች ብዛትና ለማቅረብ ውል የገቡበት የማሳ ስፋት፣ ግብርና ምርት ዓይነት፤ መጠንና የጥራት ደረጃ ማጠቃለይ የሚያሳይ መረጃ፤
8) ሚኒስቴሩ በማጠቃለያ ቅጹ የሚያካትታቸው ሌሎች መረጃዎች፤

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**13.የግብርና ምርት ውል ሃሳብን ለመመርመር የሚሰጥ የጊዜ ገደብ**

ተዋዋይ ወገኖች የውል መነሻ ሃሳብ ይዞ ለመቅረብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አስቀድመው የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል፤

1) ማንኛውም ተዋዋይ ወገን የውል መነሻ ሃሳብን ይዞ የሚቀርበው ውል ከሚገባበት የግብርና ምርት ማምረቻ ሥነምህዳር አኳያ የዘር ወቅት አንድ ወር በፊት መሆን አለበት፤
2) የግብርና ምርት ውል መነሻ ሃሳብ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመመርመር የሚወሰደው ጊዜ ከአስራ አምስት ቀናት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

14.የቋሚ ሰብል የግብርና ምርቶች የውል ዘመን፤

በባሕሪያቸው ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን የሚያስፈልጋቸው የግብርና ምርቶች ዝርዝር ሚኒስቴሩ ሰፊ ሽፋን ባለው የመገኛኛ ብዙሃን ወይም በራሱ የበይነ መረብ አድራሻ ያሳውቃል፡፡

15.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በጣሰ ሰው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው አካል የሚወሰዱ አስተዳደሪያዊ እርምጃዎች፡-

ሀ/ አስመራች ወይም ሶስተኛ ወገን በአምራቹ ላይ ላደረሰው ጉዳት በድርድር ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ማስደረግ፤

ለ/ አምራቹ አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ/አርብቶ አደር ከሆነ በግብርና ውል መሰረት በሚደረገው የአምራችና አሰመራች ግንኙነት በጽሁፍ በሚገለጽ የተወሰነ ግዜ እንዳይሳተፍ ማድረግ፤

ሐ/ አምራቹ ሰፋፊ እርሻ ያለው ሰው ከሆነ ለአስመራቹ በድርድር ላይ የተመሰረተ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ማድረግ፤

መ/ አስመራቹ ወይም አምራቹ አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይችል የነበረውን ድጋፍ ወይም ማበረታቻ እንዲያጣ ማድረግ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የሚወስደው አስተዳዳራዊ እርምጃ፤

ሀ/ የኢትዮጵያን ሕግ ሁሉ ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ/ ከመውሰዱ በፊት የተፈጸመው ድርጊት የግብርና ምርት ውልን፣ አዋጁንና ይህን መመሪያ ያልተከተለ መሆኑና ሌላኛውን ወገን የጎዳ መሆኑን ገለልተኛ በሆነ አካል በጥናት አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፤

ሐ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተዋዋይ ወገኖችን ወይም የተዋዋይ ሶስተኛ ወገንን የመደራደር መብት አለመጣሱን ማረጋገጥ አለበት፤

መ/ ለሚመለከተው ተዋዋይ ወይም ሶስተኛ ወገን አስቀድሞ በጹሁፍ መገለጽ አለበት፤

16. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ይህ መመሪያ የተደነገገባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

17.መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ግዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)
የግብርና ሚኒስቴር
ሚኒስትር